መመሪያ ቁጥር 925/2014

# የንግድ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን አገልግሎት መመሪያ

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

# መመሪያ ቁጥር 925/2014
# <u>የንግድ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን አገልግሎት መመሪያ</u>

ጥራቱን የጠበቀና ተደራሽ የሆነ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት በመላ ኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ማድረግ፤ ሕዝብን በማስተማር፣ መረጃ በመስጠትና በማዝናናት ረገድ አማራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ከመፍጠሩ ባሻገር፤ የሃሳብና የአመለካከት ብዝሃነትን በማስተናገድ በአገራችን ዴሞክራሲ ስርአትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በማመን፤

በኢትዮጵያ የሕዝብ ጥቅምን መሠረት ያደረገና ብዝሃነቱ የተረጋገጠ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎትን ማስፋፋት በማስፈለጉ እንዲሁም በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 30 መሰረት በንግድ የብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ለመሠማራት የንግድ ብሮድካስት ፈቃድ ማግኘት በማስፈለጉና የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ ሒደትን ግልፅ፣ ፍትሐዊ፣ አሳታፊ እና የሃሳብና የመረጃ ብዝሃነትን የሚያስፋፋ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 6(1)፣(5) እና 31(1)(ሐ)፣(2)፤ መሰረት የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በመስጠት ዘርፉን ማስፋፋት እንዲሁም ባለፈቃዶች የሙያዊ ሥነ-ምግባርን፣ ሕገ መንግስቱን፣ የአገሪቱን ሕጎች እንዲሁም፤ የሕዝብን ሰላም፣ ደኅንነት፣ የዜጎችን ተነፃፃሪ መብቶችና ጥቅሞች ባከበረ መልኩ በኃላፊነት ስሜት ሥራቸውን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 12(7) እና አንቀፅ 90(2) መሰረት ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ "የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 925/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1/ **"የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት ትርፍ ለማግኘት በተቋቋመ በሕግ የሰውነት መብት በተሠጠው የንግድ ድርጅት፤ በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚተላለፍ

ወይም የሚሰራጭ፣ ከምድር ወደ አየር፣ በኬብል ወይም በሳተላይት አማካኝነት የሚሠራጭ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡

2/ **"የብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት ከምድር ወደ አየር፣ በኬብል፣ በሳተላይት፣ ወይም እነዚህን በማቀናጀት ሥራ ላይ በሚውሉ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ማሰራጫዎች አማካይነት ሕዝብን ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በድምጽና በምስል በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚተላለፍ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው፡፡

3/ **"ልዩ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ብቻ ያደረገ፣ በሳተላይት አማካኝነት የሚሠራጭ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ሲሆን፣ የልጆች ፕሮግራም ቻናልን፣ የዜና ፕሮግራም ቻናልን፣ የፊልም፣ የስፖርትና መሰል ፕሮግራም ቻናልን ያካትታል፡፡

4/ **"የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃድ"** ማለት በመገናኛ ብዙሃን አዋጅና በዚህ መመሪያ መሠረት የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው በሕግ የሰውነት መብት የተሠጠው የንግድ ድርጅት ሲሆን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በማግኘት አገልግሎት የሚሰጥ በሕግ ሰውነት የተሰጠው የንግድ ድርጅትንም ይጨምራል፡፡

5/ **"ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት በአለም ዓቀፍ ሥምምነት መሠረት በአለም አቀፉ የቴሌኮሙኒኬሽን ኅብረት ለኢትዮጵያ የተመደበውን የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡

6/ **"የሳተላይት የብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት ሳተላይት ላይ በተቀመጡ ማሰራጫዎች አማካይነት የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡

7/ **"የፈቃድ አመልካች"** ማለት የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት ነው፤

8/ **"የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል"** ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ተቀብሎ፣ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ መደበኛ የሥራ ክፍል ነው፡፡

9/ **"ሀገር በቀል ይዘት"** ማለት ስፖርታዊ ክንውኖችንና ማስታወቂያን የማያካትት፣ በሃገር ውስጥ በሚገኝ የብሮድካስት አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ በሆነ ዜጋ ወይም አብዛኛዎቹ ዳይሬክተሮቹ፣ ባለድርሻዎቹ ወይም አባላቱ በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ የሆነ ዜጎች የሆኑበት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ወይም እነዚህ በጋራ ወይም እነዚህ የተጠቀሱት ግለሰቦች ቢያንስ 50 በመቶ የገንዘብ

ጥቅም ይዘው ከሌላ አካል ጋር በጥምረት በማዘጋጀት የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም፣ ሙዚቃ፣ ድራማ ወይም ዘጋቢ ፊልም ነው፡፡

10/ **"የሕዝብ ጥቅም"** ማለት ከግል ወይም ከጥቂት ቡድኖች የጥቅም ፍላጎት በተቃራኒ የማኅበረሰቡን የደኅንነት፣ የምጣኔ ሃብት፣ የባሕል፣ የፖለቲካ እና መሰል ተፈጥሮ ያላቸውን ጥቅሞች ጨምሮ የሰፊው ሕዝብ ተጠቃሚነት ነው፡፡

11/ **"ፕሮግራም ኃላፊ"** ማለት በንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ያለው የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

12/ **"የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ"** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

13/ **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፡፡

14/ **"ቁጥጥር"** ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች በሕግ መሠረት መሥራታቸውንና ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን የመከታተል፣ የማረጋገጥና የማገዝ ሥራ ነው፤

15/ **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፡፡

16/ **"አዋጅ"** ማለት የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ነው፡፡

17/ **"ተባባሪ ፕሮግራም አዘጋጅ"** ማለት ማንኛውም የሀገር ውስጥ የሚዲያ ፕሮግራም በማዘጋጀት ወይም የውጭ አገር የብሮድካስት ፕሮግራም በአገር ውስጥ የብሮድካስት አገልግሎት አማካኝነት ለማሰራጨት ከንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሰረት ፕሮግራሙን ፈቃድ ባለው የብሮድካስት አገልግሎት አማካኝነት የሚሰራጭለት ሰው ነው፡፡

18/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት ነው፡፡

19/ ሌሎች በአዋጁ የተሰጡ ትርጉሞች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

20/ ወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ የሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ወይም በአዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 3(1) እና (3) መሠረት በሌሎች ሃገራት የተቋቋሙና በኢትዮጵያ ላይ አተኩረው በሚሰሩ ከምድር ወደ አየር፣ በኬብል ወይም በሳተላይት አማካኝነት በሚሰራጭ የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው መርሆች

ይህ መመሪያ በሚከተሉት መርሆዎች የሚመራ ይሆናል፡-

1/ ለዜጎች አማራጭ የመረጃ፣ የትምህርትና፣ የመዝናኛ ምንጭ የሆኑ፣ የሕዝብ ጥቅምን መሠረት ያደረጉ፣ የዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታን፣ ብዝሃነትንና አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎቶች በመላ አገሪቱ እንዲስፋፉ ማድረግ፡፡

2/ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የማግኘት መብቱን ማረጋገጥ፡፡

3/ የንግድ ብሮድካስት የፈቃድ አሰጣጥ ሒደትና የፈቃድ መስፈርቶች ግልፅ፣ ፍትሐዊ፣ አሳታፊ፤ የመገናኛ ብዙሀን ባለቤትነትን፣ የአገልግሎቱ ተጠቃሚነትን፤ የመረጃና የሃሳብ ብዝሃነትንና ስብጥርን የሚያሰፍን እንዲሁም ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ ገደብ የማይፈጥሩ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

4/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ከመንግሥት፣ ከባለቤቶች፣ ከማስታወቂያ አስነጋሪዎች፣ ከስፖንሰሮችና ከልዩ ልዩ አካላት ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ ሆነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምን የመረጃ ተደራሽነት መብት የሚያረጋግጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡

5/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች የሙያውን ሥነ-ምግባር፣ ሕገመንግስቱን፣ የአገሪቱን ሕጎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምን አክብረው መስራታቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 5. የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ባለቤትነት መብት

1/ የአክስዮን ድርሻው ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ዜጋ ወይም ድርጅት የተያዘ፤ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት የንግድ ብሮድካስት ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

2/ 25 በመቶ የሆነ የአክስዮን ድርሻው በውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት የተያዘ፤ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት የሳተላይት የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

3/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አንድ የንግድ ድርጅት በድርጅቱ ባለቤትነት ሥር የሚተዳደሩ አንድ የቴሌቪዥን፣ አንድ የሬዲዮ፣ አንድ የጋዜጣ፣ አንድ የመፅሔት እና አንድ የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ማቋቋም ይችላል፡፡

## 6. የንግድ ብሮድካስት ፈቃድ የማይሰጣቸው አካላት

የሚከተሉት አካላት የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸውም፡-

1/ አመልካቹ ግለሰብ ከሆነ፣

2/ የንግድ ብሮድካስት አመልካች ድርጅቱ ወይም የድርጅቱ ባለአክስዮኖች በሌላ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣና መፅሄት ውስጥ ከ25 በመቶ በላይ አክስዮን ያላቸው ከሆነ፤

3/ አመልካቹ የፖለቲካ ፓርቲ ከሆነ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ተፈጥሮ ያለው ድርጅት ከሆነ፤

4/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አመራር ከ25 በመቶ በላይ አክስዮን ያለው ከሆነ፤

5/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር በማንኛውም ደረጃ የአመራር አባል ከሆነ፤

6/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሲቪል ወይም ከፖለቲካ መብቶቹ የታገደ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሕግ ችሎታውን ያጣ ሰው ባለአክስዮን ወይም የበላይ አመራር ከሆነ፤

7/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የውጪ አገር ዜጋ ወይም በውጭ አገር ዜጎች የተቋቋመ ድርጅት ከ25 በመቶ በላይ አክስዮን ያለው ከሆነ፤

8/ አመልካቹ ድርጅት በውጭ አገር ዜጎች ወይም በውጭ አገር ሕግ የተቋቋመ ከሆነ፡፡

# ክፍል ሁለት
# የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የፈቃድ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት

## 7. አጠቃላይ

1/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም በታገደ ወይም በተሰረዘ ፈቃድ የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶችን ተጠቅሞ በንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

ለ) የይዘት አዘጋጅነት ፈቃድ ቢኖረውም ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው የሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ፕሮግራም በማዘጋጀት የሳተላይት ብሮድካስት አገልግሎት ስራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

ሐ) አንድ ባለፈቃድ የማስፋፊያ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በአንድ ፈቃድ ከአንድ ማሰራጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይችልም፡፡

መ) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ቢኖረውም በአዋጁ አንቀጽ 29 ከተዘረዘሩት የብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ መንገዶች መካከል ቀደም ሲል ፈቃድ ካገኘበት የፈቃድ አይነት በተጨማሪ ከባለሥልጣኑ ሌላ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

2/ ከምድር ወደ አየር የሚሰራጭ የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የሚሰጠው በውድድር ነው፡፡ በመሆኑም ባለሥልጣኑ የፈቃድ አመልካቾችን ለመጋበዝ በሚያስነግረው የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ መሠረት፤ ፍላጎቱ ያለው ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡

3/ የሳተላይትና ኬብል ንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካች የባለሥልጣኑን ማስታወቂያ ሳይጠብቅ፣ ያለ ውድድር፣ በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ እንዲሠጠው ማመልከት ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው ቢኖርም አመልካቹ እንዲሰጠው የሚያመለክተው ፈቃድ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ አድርጎ ከምድር ወደ አየር የሚሰራጭ ልዩ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሆነ በቅድሚያ ቦርድ ማፅደቅ ወይም በሳተላይትና በኬብል አማካኝነት የሚሰራጭ ከሆነ ባለስልጣኑ ማፅደቅ ይኖርበታል፡፡

5/ አመልካቹ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተደነገጉ መስፈርቶችን ካሟላና በውድድሩ የተሻለ ደረጃ ካገኘ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## 8. <u>የሳተላይት ንግድ ብሮድካስት ፈቃድ አመልካቾች</u>

1/ የሳተላይት ንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካች የባለሥልጣኑን ማስታወቂያ ሳይጠብቅ፣ ያለ ውድድር፣ በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ እንዲሠጠው ማመልከት ይችላል፡፡

2/ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ አድርጎ የሚሰራጭ የሳተላይት ልዩ የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካች ከሆነ ያለ ውድድር በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ እንዲሠጠው ማመልከት ይችላል፡፡

3/ ለባለሥልጣኑ የሳተላይት ብሮድካስት ፈቃድ ጥያቄ ካቀረበ ባለሥልጣኑ፤ አመልካቹ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላቱን በማረጋገጥ በ30 ቀናት ውስጥ ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡ አመልካቹ በ30 ቀናት ውስጥ ፈቃድ ካልተሰጠው ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማመልከት በ15 ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡ የበላይ ኃላፊው በተጠቀሰው ጊዜ ምላሽ ካልሰጠ አመልካቹ በ30 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማመልከት ይችላል፡፡

## 9. ከምድር ወደ አየር የሚሰራጭ የንግድ ብሮድካስት ፈቃድ አመልካቾችን ስለመጋበዝ

1/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) ውስን የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለመስጠት የፈቃድ አመልካቾችን ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ፣ በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ እና በሌላ የመገናኛ ብዙሃን በሚሠራጭ ማስታወቂያ የመጋበዝ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ለ) በየበጀት አመቱ ዝግጁ የሆኑ የብሮድካስት የሬዲዮ ሞገዶችን መረጃ ከሚመለከተው ተቋም ይወስዳል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወጣው ማስታወቂያ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) ፈቃድ ለመስጠት የታሰበውን የብሮድካስት አገልግሎት አይነት፤

ለ) አገልግሎቱ የሚሸፍነውን የፈቃድ ክልል ወይም አካባቢ፤

ሐ) ዝግጁ የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ፤

መ) የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች፤

ሠ) አንኳር የፎርማት ግዴታዎች፤

ረ) ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

ሰ) ፈቃድ የሚሰጥባቸው መስፈርቶች፤

ሸ) የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜና ቦታ፤ እና፣

ቀ) የማመልከቻና የፈቃድ ክፍያ መጠን፡፡

3/ አመልካቾች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው ማስታወቂያ በሚጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከደጋፊ ሠነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ያቀርባሉ፡፡

4/ የብሮድካስት ፈቃድ አመልካቾች የስራ እቅድ ሰነዶቻቸውን ለማቅረብ ለሬዲዮ የ3 ወር፣ ለቴሌቪዥን የ9 ወር ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

5/ የባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ማመልከቻዎችን ለመገምገም አስፈላጊ ነው የሚለውን ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ አመልካቾችን ይጠይቃል፤ አመልካቾች በፍትሐዊነት መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ተመሳሳይና በቂ መረጃ ይሰጣል፤

## 10. ስለፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ

1/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፤ የማመልከቻ ቅፆችንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ እንዲሞሉ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

ሀ) የአመልካቹ ወይም የጣቢያው መጠሪያ ስምና አድራሻ፣

ለ) ድርጅቱ የተቋቋመበት አገር እና የባለአክስዮኖቹ ስም፣ አድራሻ፣ የአክስዮን ድርሻ መጠንና ዜግነት፣

ሐ) ድርጅቱና የድርጅቱ ባለአክስዮኖች በሌላ ጋዜጣ፣ መፅሄት፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ያላቸው የአክስዮን ድርሻ መጠን፣

መ) የብሮድካስት አገልግሎቱ ዓላማ፣ የፕሮግራሙ አይነት፣ የሚሰራጭበት ቋንቋ፣ የሥርጭት ቀን፣ ሰአትና አጠቃላይ ሁኔታ፣

ሠ) ለስርጭቱ የሚውለውን የመሣሪያ አይነትና ጉልበት፣

ረ) ለማቋቋም የተጠየቀው የሬዲዮ ሞገድ አይነት፣

ሰ) ስርጭቱ የሚሸፍነው አካባቢ፣

ሸ) አገልግሎቱ የሚሰጥበትን፣ የማሰራጫ መሳሪያው የሚተከልበትን ወይም የሚቋቋምበትን ቦታ፣ እና

ቀ) ጣቢያውን ለማቋቋምና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገውን የገንዘብና የካፒታል መጠን፣

በ) ሌሎች አገልግሎቱን እና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎችን፡፡

2/ አመልካቹ ስርጭቱን በሳተላይት አማካኝነት የሚያሰራጭ ከሆነ በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ (1) ከተመለከተው በተጨማሪ፡-

ሀ) የሚጠቀምበትን የሳተላይት መጠሪያ ስም፣ የሳተላይት አከራዩ ባለቤት ስም፣ አድራሻ፣ የተደረገ ውልና መሰል መረጃ፣

ለ) አመልካቹ ለስርጭቱ የሚጠቀምበትን የሬዲዮ ሞገድ መጠሪያ ቁጥር፣

ሐ) ሌሎች አገልግሎቱን እና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎችን፡፡

## 11. ከማመልከቻ ቅፅ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች

አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች በማሟላት ከማመልከቻ ቅፁ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው መሆኑን የሚያስረዳ በሠነዶች አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠ የመመሥረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የንግድ ምዝገባ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

2/ የአገልግሎትና የቴክኒክ ሁኔታን የሚገልፅ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ፣

3/ ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልግ የገንዘብና የካፒታል አቅምና ምንጭ ማስረጃ፣

4/ የጣቢያው ድርጅታዊ መዋቅር ሰነድ፣

5/ የጣቢያውን ሥራ የሚመሩ የሥራ መሪዎች፣ የፕሮግራም ኃላፊዎችና የባለሙያዎች የሰው ሀይል ዝርዝር፣ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

6/ የማሰራጫ አንቴና፣ ዲሽ ወይም መሳሪያ የሚገኝበት መልከአምድራዊ መረጃ፣

7/ የብሮድካስት አገልግሎቱ ዓላማ፣ የፕሮግራሙን አይነት፣ የሚሰራጭበት አገራዊ ቋንቋ ብዛት፣ የሥርጭት ቀን፣ ሰአትና አጠቃላይ ሁኔታ፣ የሚያስረዳ ሰነድ፣

8/ ለአገር በቀል ይዘትና ለውጭ አገር ፕሮግራም እና ሙዚቃ የተመደበው የስርጭት ጊዜ መጠን፣

9/ አመልካቹ ስርጭቱን በሳተላይት አማካኝነት የሚያሰራጭ ከሆነ ከላይ ከተመለከተው በተጨማሪ፤ ከሳተላይት አገልግሎት ሰጪው ጋር የተደረገ ማንኛውም አይነት ስምምነት ወይም ደብዳቤና አመልካቹ ለስርጭቱ የሚጠቀምበትን የሬዲዮ ሞገድ መጠሪያ ቁጥር፣

10/ ሌሎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎትንና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎች፡፡

## 12.ስለመጀመሪያ ማጣሪያ እና ተቀባይነት ስለሌለው ማመልከቻ

1/ የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍሉ በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 8 እስከ አንቀፅ 11 የቀረበለትን ማመልከቻ እና ደጋፊ ሰነድ በመመርመርና የመጀመሪያ ማጣሪያ በማድረግ አመልካቹ፡-

ሀ) የመመሥረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የንግድ ምዝገባ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ፣

ለ) የፋይናንስና የካፒታል አቅሙን እና ምንጩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሕጋዊ ማረጋገጫ ማስረጃ ካላቀረበ፣

ሐ) ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፣

መ) ድርጅቱ በግለሰብ የተቋቋመ፣ ድርጅቱ በውጭ አገር ዜጎችና ድርጅቶች ብቻ የተቋቋመ ከሆነ፣ በድርጅቱ አክስዩን ውስጥ የውጭ ዜጎችና ድርጅቶች ድርሻ ከ25 በመቶ በላይ ከሆነ፣ እንዲሁም በአዋጁ አንቀፅ 24(2)፣ 40 እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሰረት ፈቃድ የማይሰጠው ሰው ከሆነ፤ ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ ማሳለፍ ሳያስፈልገው ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ መሠረት የመጀመሪያውን ማጣሪያ ያለፈ አመልካች ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ በመሸጋገር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የፈቃድ መስፈርቶች ማሟላቱ ተረጋግጦና ተመዝኖ ፈቃድ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

## 13.የፈቃድ መስጫ አጠቃላይ መስፈርቶች

1/ የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካትታል፡፡

ሀ) ከብሮድካስት አገልግሎት ቴክኖሎጂ እድገቶች ጋር በተያያዘ ሊሰጥ ከታሰበው አገልግሎት የሚጠበቅ የቴክኒክ ጥራትና አመልካቹ በፕሮጀክት

ሀሳበ-ሥራው የዘረዘራቸው መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፤

ለ) አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ተስማሚነት፣ ድርጅታዊ ብቃት፣ የሥራ ልምድና ሙያዊ እውቀት፤

ሐ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቅምና ምንጭ፣ አስተማማኝነትና ሥራውን ለማስኬድ ያለው ዝግጁነት፤

መ) በአመልካቹ ፕሮጀክት ሀሳበ-ሥራ የተዘረዘሩ የፕሮግራሞች መርሐግብርና በፕሮግራሞቹ የተካተቱ ማኅበራዊ ፍላጎቶች፤ ለአገር በቀል ፕሮግራምና ሙዚቃ የሰጠው ትኩረት፣

ሠ) አመልካቹ ለአገልግሎቱ የመደበው የስርጭት ጊዜ እና፣

ረ) በሕግ የሰውነት መብት በተሠጠው የንግድ ድርጅት አማካኝነት ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ፣ በማስታወቂያና ስፖንሰርሽፕ ገቢ የሚተዳደር መሆኑ፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከመንግስትና ከልዩ ልዩ አካላት ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ በሆነ የንግድ ድርጅት የተቋቋመ መሆኑ፣

2/ በአዋጁ አንቀፅ 32(1) መሰረት ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር በማድረግ ተጨማሪ የፈቃድ መስፈርቶችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14. <u>የፈቃድ መስጫ ዝርዝር መስፈርቶች እና የመገምገሚያ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት</u>

1/ የፈቃድ መስጫ ዝርዝር መስፈርቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት በሕግ የሰውነት መብት በተሠጠው የንግድ ድርጅት አማካኝነት ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ፣ በማስታወቂያና ስፖንሰርሽፕ ገቢ የሚተዳደር መሆኑና ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከመንግስትና ከልዩ ልዩ አካላት ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ በሆነ የንግድ ድርጅት የተቋቋመ መሆኑ፣ እና

ለ) የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች ብዛት፣ ስብጥርና ብዝሃነት፣

ሐ) አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው የፋይናንስና የካፒታል አቅምና ምንጭ፣ የሰው ሀይልና የድርጅታዊ አቅም፣ ብቃት፣ ዕውቀትና የሥራ ልምድ፣

መ) በፕሮጀክት ሰነዱ የተዘረዘሩትና ለስርጭት የሚውሉት የብሮድካስት መሣሪያዎች አይነት፣ የስቱዲዮ አደረጃጀት፣ የቴክኒክ ደረጃና ብቃት፣

ሠ) አገልግሎቱ የሚሰጥበት ወይም የማሰራጫ መሳሪያ፣ አንቴና ወይም ዲሽ የሚቋቋምበት መልከአ ምድራዊ ቦታ አስተማማኝነት፣

ረ) የብሮድካስት አገልግሎቱ ወይም የፕሮግራሙ አላማ፣ የፕሮግራሙ አይነት፣ የሥርጭት ቀንና ሰአት፣

ሰ) በአመልካቹ የቀረበው የፕሮግራም ይዘት፣ አላማ፣ በፕሮግራሙ የተካተቱ ማህበራዊ ፍላጎቶችና ለትምህርታዊ ፕሮግራሞች የሰጠው ትኩረት፣

ሸ) ፕሮግራሙ ለህፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሰጠው ትኩረት፣

ቀ) ፕሮግራሙ የሚሰራጭበት አገራዊ ቋንቋ ብዛት፣

በ) ለአገር በቀል ይዘት፣ ፕሮግራምና ሙዚቃ የመደበው የሥርጭት ጊዜ መጠን፣

ተ) የጣቢያው ዕለታዊ የሥርጭት ጊዜ መጠን እና የሚሸፍነው አካባቢ፣

ቸ) ለስርጭቱ የሚውለው የሬዲዮ ሞገድ፣ የሳተላይት አይነት፣ የሳተላይቱ ባለቤት ስም፣ አስተማማኝነትና ለህዝብ የሚኖረው ጠቀሜታ፣

ገ) አመልካቹ ቀደም ሲል በመገናኛ ብዙሃን ሥራ የተሰማራ ከሆነ ከሕብረተሰቡ የቀረበ ተደጋጋሚ ቅሬታና ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ተደጋጋሚ የማስተካከያ ግብረመልስ አለመኖሩ፣

ረ) በባለሥልጣኑ የበላይ አመራር እና በፈቃድ ስራ ክፍሉ ፊት በሚደረግ ቃለ መጠይቅ የሚካሄድ ምዘና የተሰጠው ነጥብ፣

አ) ሌሎች አገልግሎቱንና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎች፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 እና 9 የተዘረዘሩትን አጠቃላይና ዝርዝር የፈቃድ መስፈርቶች፤ እንዲሁም የተጠየቀውን የብሮድካስት ፈቃድ አይነት እና የማሰራጫ ቴክኖሎጂን ግምት ውስጥ በማስገባት የአመልካቾችን ብቃት በመመዘን ነጥብ ለመስጠት የሚያስችለውን የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት ሠነድ ያዘጋጃል፤ በባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማስፀደቅ ስራ ላይ ያውላል፡፡

3/ ባለሥልጣኑ ለብሮድካስት አገልግሎት የሚውል የሬዲዮ ሞገድ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ከማረጋገጥ አንፃር በምዘናና ነጥብ አሰጣጥ ከዚህ በታች ለተመለከቱት አመልካቾች የተሻለ ትኩረት ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) የተለያዩ ፍላጎቶችና ምርጫዎችን ለሚያስተናግዱ፤

ለ) የሃገር አቀፍ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ የብሮድካስት አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ሚዛን እንዲኖራቸው ለሚያግዙ፤

ሐ) ነፃና ገለልተኛ የሆኑ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች፤ እና

መ) ፈቃድ የተጠየቀበትን አካባቢ ኅብረተሰብ ፍላጎት መኖር፡፡

## 15.የንግድ ብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሂደት

የንግድ ብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርአት ሂደት የሚከተለውን የሥራ ፍሰት ጠብቆ ይከናወናል፡-

1/ ከምድር ወደ አየር የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት አመልካች ባለሥልጣኑ በሚወጣው ማስታወቂያ በሚጠቀሰው ጊዜ ውስጥ እንዲሁም የሳተላይት ብሮድካስት አመልካችም በማናቸውም ጊዜ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከደጋፊ ሠነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ያቀርባል፤

2/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመርና የመጀመሪያ ማጣሪያ በማድረግ፡-

ሀ) አመልካቹ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ በአንቀጽ 24(2)፣ 40 እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው አካል መሆኑን ካረጋገጠ፤ ማመልከቻውን በዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልገው ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆንና ውሳኔው ለአመልካቹ በጽሁፍ እንዲገለፅለት የውሳኔ ሃሳቡን ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

ለ) አመልካቹ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ማቅረቡና ፈቃድ ሊሰጠው የሚችል አካል መሆኑን ካረጋገጠ፤ በአዋጁ አንቀጽ 37 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 እና 14 የተዘረዘሩት የፈቃድ መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥና ለመመዘን ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ እንዲያልፍ ውጤቱን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

3/ የበላይ ሃላፊው ከፈቃድ ስራ ክፍሉ የቀረበለትን የአመልካቾች ዝርዝርና የውሳኔ ሃሳብ በመመርመር ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ ማለፍ የሚገባውን አመልካች በማፅደቅ ምዘናና ውድድር እንዲካሄድ ይወስናል፡፡

4/ የፈቃድ ስራ ክፍሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 የቀረበለት ማመልከቻ በአንቀጽ 11፣ 13፣ እና 14 የተዘረዘሩትን ሰነዶችና መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ፤ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14 መሰረት በተዘጋጀው የፈቃድ አሰጣጥ የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ የአሰራር ሥነ ሥርአት መሰረት የአመልካቾችን ብቃት በመመዘን አመልካቾች ያገኙትን ውጤትና ደረጃ የያዘ የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

5/ የበላይ ኃላፊው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በቀረበለት የፈቃድ ማመልከቻ ላይ አመልካቹም ሆነ ዜጎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ የበላይ ኃላፊው በፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት እንዲሁም በአመልካቹ የቀረበለትን ሠነድ፣ የሕዝባዊ አስተያየቱን

ውጤትና ሌላ መረጃ መርምሮ አመልካቹ የፈቃድ መስጫ መስፈርቶችን ማሟላቱን ሲያረጋግጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዳይሰጠው ውሳኔ ይሰጣል፡፡

7/ ባለሥልጣኑ የወሰነውን ውሳኔ፣ ለውሳኔው ያደረሱ ምክንያቶችንና ፈቃድ ሲሰጥ ተግባራዊ የሚሆኑ የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎችን ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፤ እንዲሁም በድረ-ገጹ፣ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

8/ የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታን የያዘ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ከፈረመና ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ ከከፈለ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

9/ አመልካቹ የተፈቀደለት የብሮድካስት ፈቃድ የሬዲዮ ሞገድ እና የሊንክ ሬዲዮ ሞገድን የሚጠቀም ከሆነ፤ ለአመልካቹ የሬዲዮ ሞገድ ወይም የሊንክ ሬዲዮ ሞገድ እንዲመደብለትና እንዲሰጠው ባለስልጣኑ ለኮሙዩኒኬሽን አገልግሎቶች ባለሥልጣን በደብዳቤ በማሳወቅ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

10/ የፈቃድ ምስክር ወረቀት እንዲወስድ በጽሑፍ የተገለፀለት አመልካች ደብዳቤ በደረሰው በ2 ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ በመፈፀም እና በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታ ስምምነት ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ካልወሰደ የፈቃድ ውሣኔው ይሰረዛል፡፡

11/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ቢኖርም ባለፈቃዱ የተዘጋጀውን ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ያልወሰደው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ባለሥልጣኑ የ3 ወር ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

12/ ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለንግድ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ንግድ ቢሮ በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት፡፡

## 16.<u>በፈቃድ አመልካች ላይ ሕዝባዊ አስተያየት ስለመጥራትና ለአመልካቹ ቃለመጠይቅ ስለማቅረብ</u>

1/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ለመገምገም ሕዝባዊ አስተያየት ማሰባሰብ ከፍ ያለ የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ከሆነ፤ ባለስልጣኑ ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበትን መድረክ ለመጥራት ሊሟሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማውጣት ጣቢያው በሚቋቋምበት አካባቢ ውስጥ ሕዝባዊ መድረክ ሊጠራ ይችላል፡፡

2/ አመልካቹ ፈቃድ በማግኘት አገልግሎቱን በጥራት ለማከናወን ያለውን ዝግጁነት በተመለከተ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊዎችና የፈቃድ ስራ ክፍሉ ለሚያቀርቡለት የቃል መጠይቅ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 17.<u>የንግድ ብሮድካስት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን</u>

1/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ ከምድር ወደ አየር፣ በሳተላይት ወይም በኬብል አማካኝነት የሚሠራጭ የንግድ ቴሌቪዥን አገልግሎት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን 10 አመት ይሆናል፡-

2/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ የንግድ ሬዲዮ አገልግሎት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን፡-

ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራጭ ከሆነ 10 አመት፤

ለ) የሥርጭት ሽፋኑ በክልል ደረጃ የተወሰነ ከሆነ 8 አመት፤

ሐ) የስርጭት ሽፋኑ በአካባቢ ደረጃ የተወሰነ ከሆነ 6 አመት፤

## 18.<u>የንግድ ብሮድካስት ፈቃድ እድሳት</u>

1/ ባለፈቃዱ በአንቀጽ 17 የተወሰነው የፈቃድ ዘመን ከማለቁ ከ1 ዓመት ባልበለጠና ከ6 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማሳደሻ ቅጽ ሞልቶ ማመልከቻውን በማቅረብ ፈቃዱን ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት የታደሰ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን 1(አንድ) ዓመት ይሆናል፤ ፈቃዱ በየአመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

3/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍል ፈቃዱን ከማደሱ በፊት፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን፣ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች የተመለከቱ ግዴታዎችን የማክበር የኋላ ታሪክና የተወሰዱበት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አለመኖራቸውን ከግምት ውስጥ ማስገባት፣

ለ) ባለፈቃዱ በተገልጋዩ ሕብረተሰብ ተቀባይነትን ያገኘ፣ ተደጋጋሚ የሆነ የቅሬታ ሪከርድ የሌለበት፣ በባለሥልጣኑ የሞኒተሪንግና ክትትል ውጤት ተደጋጋሚ ግድፈት ያልተገኘበት መሆኑን፣

ሐ) የሬዲዮ ሞገዱ ከፍ ላለ የሕዝብ ጥቅም አለመፈለጉን፣ እና

መ) ባለፈቃዱ በፈቃድ ዘመኑ ውስጥ አመታዊ ክፍያውን በወቅቱ ይከፍል የነበረ መሆኑን በማረጋገጥ ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

4/ የበላይ ኃላፊው የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና መረጃዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5/ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ግዴታ የያዘ ስምምነት ሠነድ በመፈረምና ለፈቃድ እድሳት የተተመነውን ክፍያ ከፍሎ የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ያገኛል፡፡

6/ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ አመልካች ጉድለቶቹ እስኪስተካከሉ ድረስ የፈቃድ ዘመኑ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ ፈቃዱ ለ3 ወራት ባለሥልጣኑ ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

7/ ማንኛውም የንግድ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቀርቦ የእድሳት ማመልከቻውን ሳያቀርብ የፈቃድ ማደሻ ጊዜው ካለፈ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ እንደተወ ተቆጥሮ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡ የብሮድካስት አገልግሎት መስጠትም አይችልም፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያላሳደሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ፣ በዚህ መመሪያ የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ያገኛል፡፡

## 19.<u>ለፈቃድ እድሳት የህዝብ አስተያየት ስለማሰባሰብ</u>

1/ የበላይ ኃላፊው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 18 የቀረበለትን የፈቃድ እድሳት የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት መርምሮ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የፈቃድ እድሳት ጥያቄ የቀረበለት መሆኑን ለህዝብ በመገናኛ ብዙሃን በማስታወቅ፣ የእድሳት ማመልከቻውን በሚመለከት የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ መድረክ ሊያዘጋጅ ወይም በጽሁፍ አስተያየት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ አመልካቹ የቀረበውን አስተያየት በሚመለከት ባለስልጣኑ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሹን በጽሁፍ እንዲያቀርብ እድል ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 20.<u>ተቀባይነት ስላላገኘ የፈቃድ ጥያቄና የፈቃድ እድሳት ማመልከቻ</u>

1/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 15(2)(ሀ)፣ (6) እና (10) መሰረት የፈቃድ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ወይም ፈቃድ እንዳይሰጥ ወይም እንዲሰረዝ ከወሰነ፣ ማመልከቻው ውድቅ የሆነበትን ወይም ፈቃዱ የማይሰጥበትን ወይም የተሰረዘበትን ምክንያት በ14 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ፣ ወይም ሰፊ ስርጭት ባለው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

ለ) በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 18 መሰረት ፈቃድ ላለማደስ የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ካመነ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ በመግለፅ በ14 ቀናት ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ አስተያየቱን እንዲሰጥና ቅሬታ ካለው በፅሁፍ እንዲያቀርብ እድል ይሰጣል፡፡ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን ምላሽ በመገምገም የአመልካቹን ፈቃድ የማያድስ ከሆነ ከ3 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በበላይ ኃላፊው ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

3/ ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና የውሳኔውን ቅጂም በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

4/ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

## 21.የሥርጭት አገልግሎትን ለማስፋፋት የማስፋፍያ ፈቃድ ስለማስፈለጉ

1/ ማንኛውም ባለፈቃድ የሥርጭት አገልግሎቱን ለማስፋት የሚከተሉትን ለውጦች ለማድረግ ሲፈልግ፤ መሳሪያው የሚተከልበትን ቦታ ከአስፈላጊ ዝርዝር መረጃ ጋር በማቅረብ በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

ሀ) የስርጭት አገልግሎት ከሚሰጥበት አካባቢ ውጪ ሌሎች አካባቢዎችን ለማዳረስ፤ ተጨማሪ ስርጭት ለማካሄድ ወይም ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ ለማግኘት፣

ለ) የማሰራጫ መሣሪያውን ጉልበት ከተፈቀደው መጠን ለመለወጥ፣ ቦታ ለመቀየር፣ የጣቢያውን አቅም ለማሳደግ፣

ሐ) የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማድረግ፣ እና

መ) የአንቴናውን ዓይነትና ተሸካሚ ምሰሶውን ርዝመት ወይም ቦታ ለመቀየር፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሰረት የማስፋፊያ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፡-

ሀ) ፈቃድ በተጠየቀበት አካባቢ የተመዘገበ በቂ የሬዲዮ ሞገድ መኖር አለመኖሩንና የማስፋፊያ ፈቃድ የተጠየቀበት የሬዲዮ ሞገድ በሌላ የብሮድካስት አገልግሎት አለመያዙን ወይም ለሌላ አገልግሎት አለመፈለጉን፣

ለ) የተመረጠው የማስፋፊያ ቦታ ለታቀደው አገልግሎት ተስማሚ መሆኑን፣

ሐ) አገልግሎቱን ለማስፋፋት የቀረቡት መሣሪያዎች ከታቀደው የአገልግሎት ማስፋፊያ ጋር መጣጣማቸውን፣

መ) የሌሎች የመገናኛ አገልግሎት መሣሪያዎችን ሥራ የማያውክ መሆኑን፣ እና

ሠ) ፈቃድ የተጠየቀበትን አካባቢ ኅብረተሰብ ፍላጎትና የሕዝብ ጥያቄን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## 22.የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች

1/ ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፤ ባለፈቃዱ ፈቃድ ለማግኘት ሲል በማመልከቻው የገለፀውን የፈቃድ ሁኔታ እና ባለፈቃዱ ሊከተለው የሚገባ ግዴታን መሠረት ያደረገ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ያዘጋጃል፤

2/ ያዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታ የሥምምነት ሰነድ አመልካቹ እንዲያገኛቸው፣ አስተያየቱን የመግለፅ እድል እንዲሰጠው እና የስምምነት ሠነዱን በመፈረም ፈቃድ እንዲሠጠው ያደርጋል፡፡

3/ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው ላይ የገለፀው የፈቃድ ሁኔታና የፈቃድ ስምምነት ሠነድ የፈቃድ ግዴታዎች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡

4/ የፈቃዱ ሁኔታዎችና ግዴታዎች እንደ ፈቃዱ አይነት ሊለያዩ የሚችሉ ቢሆንም፤ የሚከተሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች ያካትታል፡-

ሀ) አገልግሎቱ የሚሸፍነውን የፈቃድ ክልል፤

ለ) የቴክኒክ መስፈርቶች መዘርዝር፤

ሐ) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ሥርጭት የሚጀምርበት ጊዜና ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

መ) የፈቃድ ማደሻ ሁኔታዎች፤

ሠ) የአገልግሎት ክፍያ መጠን፤

ረ) የፕሮግራም ፎርማት ግዴታዎች፤

ሰ) የፕሮግራም የይዘት ደረጃዎች፤

ሸ) የፈቃድ ሁኔታዎች ሲጣሱ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች፤

ቀ) ባለሥልጣኑ በመደበኛነትና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸው የመረጃ አይነቶች፤

በ) ፈቃድ የሚሻሻልባቸው ሁኔታዎች፤ እና፣

ተ) ቅሬታዎችና አለመግባባቶች የሚያዙበትና እልባት የሚያገኙበት መንገድ፤ የሚሰጡ መፍትሔዎችና እርምቶች፤

ቸ) ስለ አገልግሎትና የተጠቃሚዎች መብት የሚሰጥ መረጃ ግልፅነት፤

## ክፍል ሦስት
## የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃድ መብቶች እና ግዴታዎች

### 23.የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃድ መብቶች

1/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዶች በከፍተኛ ሥነ-ምግባር ተግባራቸውን የማከናወን፣ ነፃና የተለያዩ አመለካከቶች የሚንጸባረቁበት ምህዳርን የመፍጠር እና ለሃሳብ ልውውጥ መጎልበት አስተዋፅኦ የማድረግ መብት አላቸው፡፡

2/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዶች ተግባራቸውን በብቃት ለመፈጸም በሚያስችላቸው ሁኔታ በይዘት፣ በአደረጃጀታቸውና በበጀታቸው ከመንግሥት፣ ከፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር ተጽእኖዎች ነፃ የመሆን መብት አላቸው፡፡

3/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ኤዲቶሪያል ነፃነት የተጠበቀ ነው፤ በሥራውም ሆነ በአስተዳደር መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ ነው፡፡

4/ በሕግ በግልፅ ከተመለከተው አግባብ ውጪ በብሮድካስት ስርጭት ላይ የይዘት ግዴታዎች አይጣሉም፡፡

5/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዶች ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፤ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ወይም ትችት የማቅረብና ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችን፣ መሣሪያዎችን የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

6/ ባለፈቃዱ ሕገ መንግሥቱን በመፃረር የፕሬስ ነፃነትን የሚያደናቅፍ አሰራር ከተፈፀመበት ለባለሥልጣኑ ሥራ አመራር ቦርድ ወይም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

7/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዶች በመረጡት ሕጋዊ መንገድ የመደራጀት መብት አላቸው፡፡

8/ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ አንቀፅ 49 ከተመለከተው ውጪ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ለመገናኛ ብዙሃን ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡

9/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ በግልፅ የተመለከቱ መስፈርቶችን በማሟላት ፈቃድ፣ የማስፋፊያ ፈቃድ እና የፈቃድ እድሳት የማግኘት መብት አለው፡፡

10/ ባለስልጣኑ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዶች መብቶች ተግባራዊነት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡

## 24.ፕሮግራም፣ ዜና እና ማስታወቂያን በሕግ አግባብ የማሰራጨት ግዴታ

1/ በንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ፕሮግራም፣ ዜና ወይም ማስታወቂያ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) ሕገ መንግስቱን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁን፣ የማስታወቂያ አዋጁን፣ የሙያውን የስነ-ምግባር መመሪያ፣ ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ የወጡ ሕግጋትን እና ሌሎች የአገሪቱን ሕጎች ማክበር፣

ለ) የተለያዩ አመለካከቶችን በማንፀባረቅ አጠቃላይ ሕብረተሰቡን የሚያገለግሉ ሚዛናዊና ከአድልዎ የፀዳ መሆን፣

ሐ) የፕሮግራምና ዜና ይዘትና ምንጭ እውነተኛ፣ ትክክለኛ፣ ፍትሐዊና ከአድልኦ የጸዱ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግና ስህተት ሲገኝም ማረም፡፡

2/ በብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ፕሮግራም ወይም ዜና፣

ሀ) የማንኛውንም ሰው የግል ሕይወት የመከበር መብትን የሚጥስ፣

ለ) የሰው ልጆችን ክብር የሚፃረር፣

ሐ) ለጤናና ለደኅንነት ጎጂ የሆነ ባህሪን የሚያበረታታ፣

መ) የወንጀል ድርጊት እንዲፈጸም፣ ሰላምና ፀጥታ እንዲደፈርስ የሚቀሰቅስ፣

ሠ) ማንኛውም የሰው ዘርን፣ ቋንቋን፣ ዜግነትን፣ ብሔርን፣ ቀለምን፣ ኃይማኖትን፣ ሥርአተ ጾታን፣ እድሜን ወይም የአእምሮ በሽታንና የአካል መጉደልን መሰረት በማድረግ እንዲጠላ፣ ጥቃት እንዲደርስበት ወይም እንዲገለል የሚቀሰቅስ፣

መሆን የለበትም፡፡

3/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ጥቃት ወይም ሌላ አሰቃቂ ወይም አስደንጋጭ ሁኔታዎችን የሚዘግቡ ዜና ወይም ፕሮግራሞችን ሲያሠራጭ በአቀራረባቸው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4/ ፕሮግራምና ዜና በጣቢያው ከመሠራጨቱ በፊት ሕግን የሚያከብር መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

5/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን አመለካከትና ስነልቦና ሊጎዳ የሚችል ፕሮግራምን ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 11 ሰዓት ካለው ሰዓት ውጪ ማስተላለፍ የለበትም፡፡

6/ የኃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞችን የሚያሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በኃይማኖቶች ተከታዮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት ማነሳሳት፣ የሌሎችን ኃይማኖት ወይም እምነት ማንኳሰስ፣ ወይም በኃይማኖቶች ተከታዮች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር መቀስቀስ የለበትም፡፡

## 25. የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች

በአዋጁ አንቀፅ 31(2) መሠረት ትኩረቱን በአንድ ጉዳይ ላይ አድርጎ እንዲዘግብ የተፈቀደለት ካልሆነ በስተቀር፣ ትርፍ የማግኘት ዓላማን ይዞ መቋቋሙ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1/ በፈቃድ አካባቢ የሚገኙ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች የማገልገል፣

2/ በዕለቱ ፕሮግራም ውስጥ አገራዊ፣ አካባቢያዊና ክልላዊ ወቅታዊ ዜናዎችንና ውይይቶችን ያካተቱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣

3/ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ብዝሃነት፣ ፍላጎትና ስሜት የሚያንጸባርቅና የሚያስተናግዱ መረጃ ሰጪ፣ አስተማሪና አዝናኝ ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣

4/ ዴሞክራሲያዊ የግልፅነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን ጨምሮ የማኅበረሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ መረጃዎችንና ፕሮግራሞችን ለሕዝብ የማቅረብ፣

5/ በፈቃዱ አካባቢ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ባህል የሚያበረታቱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣ ለአገራዊ ባህልና ቋንቋዎች ፍትሃዊ ሽፋን መስጠት፣ ማበረታታትና ሕብረ-ብሔራዊ ማንነት መጎልበቱንና መጠበቁን የማረጋገጥ፣

6/ በከፍተኛ መጠን ሀገር በቀል ይዘት ያላቸውን ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣ እና፣

7/ የኢትዮጵያ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ድራማዎችን፣ ዘጋቢ ፊልሞችንና የሕፃናት ፕሮግራሞችን የማካተት፡፡

8/ የኢትዮጵያ የተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ፍትሃዊ ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፣ ለአካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ የተዘጋጁ የፕሮግራም ይዘቶችን የማሰራጨት፣

9/ ለአገራችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግና፣ እንዲሁም በሕገ መንግሥቱና በሌሎች የሕዝብ ጥቅምና የጋራ አገራዊ እሴቶች እንዲጠናከሩ አስተዋፅኦ የሚያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት የመስጠት፣

10/ የማኅበረሰቡን ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሠረቶች የሚጠብቁ፣ የሚያጠናክሩና የሚያሳድጉ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣

11/ በፕሮግራም ሥርጭቱ ተገቢና ጨዋ የቋንቋ አጠቃቀም ተግባራዊ የማድረግ፣

12/ በፕሮግራም መርሀ-ግብሩ መሰረት ፕሮግራሞችን የማሠራጨት፣ በመርሀ ግብሩ መሠረት ማሠራጨት ካልተቻለ አስቀድሞ የማሳወቅ፣

13/ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተያያዙ አወዛጋቢ ወይም አከራካሪ ጉዳዮችን ሽፋን ሲያገኙ በተመሳሳይ ፕሮግራም ወይም በሌላ ቀጣይ ፕሮግራም የተለያዩ አመለካከቶችን ለማስተናገድ ምክንያታዊ ጥረት የማድረግ፣

14/ ዴሞክራሲያዊ፣ በመረጃ የበለጸገ፣ አዲስ ነገር ለመቀበል ዝግጁ የሆነ፣ ሳይንሳዊ ፈጠራን የሚያበረታታ፣ ቻይና ታጋሽ የሆነ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር የሚያበረታቱና በሃገር ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን፣ ሃገራዊ ልምዶችንና መዳረሻ ግቦችን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

15/ በእኩልነት ሕገ-መንግሥታዊ መርህ፤ የተለያዩ ሃሳቦች፣ ፍላጎቶች፣ እምነቶችና አይታዎችን የማስተናገድ፤

16/ የሁሉም ኢትዮጵያዊያንን መረጃና ሃሳብ የመቀበልና የማሰራጨት መብትን የማረጋገጥ፤

17/ በባለፈቃዶች መካከል የሚደረግ የፕሮግራም ልውውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የፕሮግራም "ቻናል" ብቻ ፕሮግራሙን የማሠራጨት፤

18/ በቀጥታ ሥርጭት በቴሌቪዥን የሚሠራጩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ፕሮግራሞችን ሲያቀርብ የፕሮግራሙን ይዘት በምልክት ቋንቋ የማቅረብ፤ እና፣

19/ በቴሌቪዥን አገልግሎት በጽሁፍ የሚያቀርባቸውን አስፈላጊ መረጃዎች በድምጽ አስደግፎ የማቅረብ፡፡

20/ የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት የሚያናጋ ሁኔታ ወይም የተፈጥሮ አደጋ በማጋጠሙ ወይም የሕዝቡን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረርሽኝ በሽታ፤ በመከሰቱ ምክንያት የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት የሚሰጠውን አስቸኳይ መግለጫ ያለክፍያ የማሠራጨት፡፡

## 26. <u>የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ አስተዳደራዊ ግዴታዎች</u>

የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ተግባር፣ ሃላፊነቶች መከናወናቸውን ያረጋግጣል፡-

1/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተደራሽነትን ለማበረታታት በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ባለፈቃዶች ጋር መተባበር፤

2/ ለሚያስመጣቸው የብሮድካስት መሳሪያዎች በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የማረጋገጫ ሠርተፍኬት የማግኘት፤

3/ የተመደበለትን የሬዲዮ ሞገድ ለሌላ አላማ ያለማዋል፤

4/ ጣቢያው በአገር ውስጥ የሚቀጥራቸው ባለሙያዎች የውጭ አገር ዜጎች ከሆኑ በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል የስራ ፈቃድ ያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ፣

5/ የአለምአቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት በየጊዜው የሚያወጣውን ደንብ ማክበር፤

6/ በእያንዳንዱ ፕሮግራም መጀመሪያና መጨረሻ ላይ የጣቢያውን ስም፣ ምልክት እና ፕሮግራሙ የተላለፈበትን ቀንና የፕሮግራሙን ኃላፊና አዘጋጅ ስም መግለጽ፤

7/ ለሚያሠራጨው ፕሮግራም እና ዜና ኃላፊ አድርጎ የሚመድበውን ሰውና የሃላፊነት ድርሻ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፤

8/ ማስታወቂያንና ዜናን ጨምሮ ያሰራጨውን ማናቸውም ፕሮግራም ለ30 ቀናት ቀርጾ ማስቀመጥ፤ በተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበም ቅሬታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ፕሮግራሙን ይዞ ማቆየትና በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው አካል ለቁጥጥር ወይም የቀረበ ቅሬታን ለመመርመር ሲጠይቅም ቅጂውን በራሱ ወጪ ማቅረብ፤

9/ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ተባባሪ ፕሮግራም አዘጋጆች የብቃት ማረጋገጫና የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

## 27.<u>አገርበቀል ፕሮግራም እና ሙዚቃ የማሠራጨት ግዴታ</u>

1/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ለዜና፣ ለወቅታዊ ጉዳይ፣ ለትምህርታዊ፣ ለመዝናኛና ለሌሎች ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ተገቢውን የአየር ሰአት መመደብ ይኖርበታል፡፡

2/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው 60 በመቶውን ፈቃድ የወሰደበት አካባቢን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ ክልላዊ እና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

3/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሙዚቃ ሥርጭት ጊዜው ቢያንስ 60 በመቶውን ለአገራችን ሙዚቃዎች ማዋል አለበት፡፡

4/ በሳተላይት አማካኝነት የሚሰራጭ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ አድርጎ የሚሰራጭ ልዩ የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው ቢያንስ 80 በመቶውን ፈቃድ ለወሰደበት የፕሮግራም አይነት እና ፈቃድ የወሰደበት አካባቢን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡ ሌሎች የፕሮግራም አይነቶችን ከማሰራጨት ግዴታ ነፃ ይሆናል፡፡

5/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከአመታዊ የሥርጭት ጊዜው እስከ 10 በመቶውን ከባለፈቃዱ ገለልተኛ በሆኑ ይዘት አመንጪዎች ለሚዘጋጅ ሃገር በቀል ፕሮግራሞች፣ ሙዚቃዎች፣ ድራማዎች ወይም ዘጋቢ ፊልሞች ዝግጅት ማዋል ይኖርበታል፡፡

6/ ባለስልጣኑም አፈፃፀሙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 28. የምርጫ ወቅት መግለጫዎችን የማሠራጨት ግዴታ

የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ፡-

1/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ዓላማቸውንና ፕሮግራሞቻቸውን ለሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ወይም መግለጫ እንዲያስተላልፉ በምርጫ ወቅት በሚወጣ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም መመሪያ መሠረት ነፃ የአየር ጊዜ መመደብ አለበት፡፡

2/ በምርጫ ወቅት በሚያቀርባቸው የዜና ዘገባዎች፣ ትንተናዎችና የውይይት መሰናዶዎች የመራጮችና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ድምፅ በአግባቡና በፍትሃዊነት ማካተት ይጠበቅበታል፡፡

3/ የምርጫ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተመደበላቸውን የአየር ሠአት በብቃት እንዲጠቀሙበት አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 29. ለውጦችን ስለማሳወቅና ስለማስፈቀድ

1/ የንግድ ብሮድካስተሩ የሚከተሉትን ለውጦች ባደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲጀመር፤

ለ) የሥርጭት አገልግሎቱ ለ1 ወር ሲቋረጥ፤

ሐ) የፕሮግራም መርሀ ግብርና የሥርጭት ሰዓት ለውጥ ሲያደርግ፤

መ) የጣቢያው ስም፣ ምልክትና አድራሻ ላይ ለውጥ ሲያደርግ፤

ሠ) የጣቢያው ሥራ አስኪያጅ ወይም የቦርድ አባል ወይም የፕሮግራም ኃላፊ ሲለውጥ፤

ረ) ፈቃድ ለመውሰድ ባቀረባቸው ወይም በተፈቀደለት የብሮድካስት የማሠራጫ መሣሪያ አይነት ወይም ሌሎች ጉዳዮችና መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያደርግ፣

2/ ባለሥልጣኑ የተደረገው ለውጥ በሕግ አግባብ መከናወኑን ይገመግማል፡፡

3/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ከማድረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ በፅሁፍ ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት አለበት፡-

ሀ) የሬዲዮ ሞገድ፣ የማሰራጫ መሣሪያውን ጉልበት፣ የአንቴናና መሰል መሳሪያ በተመለከተ ለውጥ ለማድረግና ቦታ ለመቀየር ሲፈልግ፣

ለ) የውጭ አገር ወይም የአገር ውስጥ ብሮድካስተሮች የሚያስተላልፉትን ዜና ወይም ፕሮግራም ተቀብሎ በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ለማሰራጨት ሲፈልግ፣

ሐ) ከሳተላይት ድርጅቶች ጋር ያደረገውን ስምምነት ለማሻሻል፣ ወይም ለማቋረጥና ፈቃድ ካገኘበት ሳተላይትና ሬዲዮ ሞገድ ውጪ በሌላ ሳተላይትና ሬዲዮ ሞገድ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን ለማሰራጨት ሲፈልግ፡፡

4/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3(ለ) መሰረት የውጭ አገር ፕሮግራሙ የሚሰራጭለት አካል የፕሮግራም ዝግጅት የብቃት ማረጋገጫና የንግድ ፈቃድ ማውጣታቸውን እና መስፈርቱን ማሟላታቸውን አረጋግጦ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

## 30.<u>አመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ስለማቅረብ</u>

1/ ባለፈቃዱ የጣቢያውን የሥራ አመራርና ሠራተኞች፣ ተባባሪ አዘጋጆች፣ ዓመታዊ የበጀት እቅዶች፣ የሂሣብ መዝገብና ዓመታዊ የስራና የሒሳብ ሪፖርት በተመለከተ መረጃ የመያዝ፣ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ሪፖርቶች የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሀ) የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክት የሥራ ክንውን ሪፖርት፣

ለ) የጣቢያውን የፋይናንስ ምንጭ ማስረጃ እና ዓመታዊ የወጪና ገቢ ሪፖርት፣ የኦዲት ሪፖርት፣

ሐ) የተባባሪ የፕሮግራም አቅራቢዎች ተገቢ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የስም ዝርዝርና የሚያሠራጩትን የፕሮግራም ዓይነትና ተዛማጅ ማስረጃዎች፡፡

3/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ ከውጭ የተገኘን ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ከውጭ አገር በእርዳታ ወይም በስጦታ መልክ ከመቀበሉ በፊት በቅድሚያ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ማስፈቀድ አለበት፡፡

4/ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን መረጃና ሪፖርት ባግባቡና በጥንቃቄ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

## 31.<u>የጣቢያውን ኢዲቶሪያል መመሪያ ስለማውጣትና ተግባር ላይ ስለማዋል</u>

1/ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ሕገ መንግስቱን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁን፣ የሙያውን ሥነ-ምግባር መሰረት ያደረገ ጣቢያው የሚመራበትን የኤዲቶሪያል ፖሊሲ ወይም መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ኤዲቶሪያል መመሪያውንም ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2/ በኢዲቶሪያል መመሪያ ውስጥ አገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር አቅጣጫዎችን በማካተትና የአገሪቱን ሕጎችና ሙያዊ ሥነ-ምግባር መሠረታዊ መርሆችን በመከተል ተግባርና ኃላፊነቱን በብቃት መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

## 32.እርማት ወይም መልስ የመስጠት ግዴታ

1/ በንግድ ብሮድካስት አገልግሎት በተላለፈ ፕሮግራም መብቴ ተነክቷል ወይም ፕሮግራሙ በአግባቡ አልቀረበም በማለት ቅሬታውን ለጣቢያው የሚያቀርብ ሰው ሲኖር፤ ባለፈቃዱ የቅሬታ አቅራቢውን መብት ሊያከብርለት እና ለጣቢያው የሚያቀርበውን እርማት በፅሁፍ በደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ በተመጣጣኝና በተመሳሳይ የአየር ጊዜ ያለ ክፍያ ሊያስተላልፍለት ይገባል፡፡

2/ ጣቢያው እርማቱን ለማስተላለፍ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ካመነበትም ከ3 ሳምንት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ እርማቱን ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን የዘገየበትን ምክንያትም በስልክ ወይም በደብዳቤ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት።

3/ እርማት የማውጣት ወይም መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ሰው ጣቢያው ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ወይም ለባለሥልጣኑ ወይም ለባለሥልጣኑ ሥራ አመራር ቦርድ ወይም ለመገናኛ ብዙሃን ካውንስል ማመልከት ይችላል፡፡

4/ ባለፈቃዱ በሚያሠራጨው ኘሮግራም ወይም ዜና ስህተት ሲገኝ ለማረም የሚያስችለውን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

5/ ባለፈቃዱ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥነ ሥርዓት በመዘርጋት ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብ ጥቆማ እና ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡

## 33.ጥቆማ፣ ቅሬታንና ግብረ መልስን ስለማስተናገድ

1/ ባለፈቃዱ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥነ ሥርዓት በመዘርጋት ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብ ጥቆማ እና ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡

2/ ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ ለሚቀርብለት ግብረ መልስ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የወሰደውን ማስተካከያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3/ ባለፈቃዱ በየ6 ወሩ የጥቆማ እና ቅሬታ አቅራቢዎችን ስም፣ አድራሻ፣ የቀረቡለትን ጥቆማና ቅሬታዎች ብዛት፣ ምክንያት፣ ለጥቆማው ወይም ለቅሬታው የሰጠውን ምላሽና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

4/ ባለፈቃዱ ከሚሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት ጋር በተያያዘ በማናቸውም ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ከተወሰነበት የአቤቱታውን ብዛት፣ ምክንያት፣ የተሰጠውን ውሳኔና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ ባለስልጣኑ ባለፈቃዶች የራሳቸውን የቅሬታ እና ጥቆማ አቀራረብ ስርዓት ተከትለው መስራታቸውን ይቆጣጠራል፡፡

## 34. የብሮድካስት አገልግሎት ክፍያዎችን ስለመክፈል

1/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃድ ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ መሰረት የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ፣ የፈቃድ ክፍያ፣ አመታዊ ክፍያ ወይም የሬዲዮ ሞገድ ክፍያ እና የፈቃድ ማደሻ ክፍያ ይከፍላል፡፡

ሀ) የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ አመልካቹ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ሲያቀርብ ይከፍላል፡፡

ለ) የፈቃድ ክፍያ አመልካቹ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ከመውሰዱ በፊት ይከፍላል፡፡

ሐ) ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ ይከፍላል፡፡

2/ ባለፈቃዱ የመንግስት በጀት አመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ አመታዊና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያውን ካልከፈለ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር 5 በመቶ መቀጫ እየታከለበት ይከፍላል፡፡ ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ 50 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የሚፈለግበትን አመታዊና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያውን አጠቃሎ ከከፈለ ባለስልጣኑ መቀጫውን ሊያነሳለት ይችላል፡፡

4/ የክፍያው መጠን በመንግስት በሚጸድቀው ተመን መሰረት የሚወሰን ሲሆን ክፍያው በባለስልጣኑ በየጊዜው እየተጠና በመንግስት ይወሰናል፡፡

## 35. ቁጥጥር እንዲደረግ ስለመፍቀድ

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡት ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፡፡

2/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ወደ ሚያደርግበት ሥፍራ ለመግባት የመታወቂያ ወረቀቱን እና ከባለሥልጣኑ ቁጥጥር እንዲያደርግ የተጻፈለትን ደብዳቤ በመያዝ በንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ጣቢያ በስራ ሰአት ለመግባትና ቁጥጥር ለማድረግ ይችላል፡፡

3/ ለክትትል እና ቁጥጥር ያመች ዘንድ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የሥራ ቦታውን እና የማሰራጫ ጣቢያውን ክፍት ያደርጋል፤ በኢንስፔክተሩ የሚጠየቀውን የሰነድ ቅጅም ያቀርባል፤

4/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ሲያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዱ መታደሱን፣ አግባብ ያላቸውን ሰነዶችና የፕሮግራም ቅጅዎች መያዛቸውን፣ የአዋጁና የመመሪው ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማየትና ቅጅ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡

## 36. <u>ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>

1/ ባለፈቃዱ ሥራውን ማካሄድ ካልቻለ ፈቃዱን በመመለስ ለባለሥልጣኑ በማመልከት ሲፈቀድለት መሣሪያውን ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2/ ፈቃዱን ለማስተላለፍ ጣቢያውንም ሆነ የጣቢያውን የአክስዮን ባለድርሻዎች የአክስዮን ድርሻ መጠን ለመጨመር፣ ለመቀነስ፣ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ፣ ሌላ የመገናኛ ብዙሃንን ድርጅትን ወይም አክስዮንን ለመግዛት፣ ለመዋሀድ ወይም መሰል ለውጥ ለማድረግ ወይም ከንብረት ይዞታ ጋር የተያያዙ ውሎችን ለማሻሻል፣ ለመለወጥ፣ ወይም ለመሰረዝ የሚፈልግ ባለፈቃድ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማመልከትና ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

3/ ባለፈቃዱ አስቀድሞ ከባለሥልጣኑ በፅሁፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር፡-

ሀ) ፈቃዱን ማከራየት፣ በሽያጭም ሆነ በሌላ መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤

ለ) የፈቃድ ቁጥርን መለወጥ፤

ሐ) በፈቃዱ የተሠጡትን መብቶችና የፈቃድ ሁኔታው ላይ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን እንዲሁም የአክሲዮን ድርሻውን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም፡፡

4/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱ እንዲተላለፍ የሚፈቅደው ፈቃድ የሚተላለፍለት ድርጅት የሚከተሉትን ሲያሟላ ይሆናል፡-

ሀ) ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው የፈቃድ ዘመኑ እስኪጠናቀቅ ድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በቂ የፋይናንስና የቴክኒክ አቅም ያለው ከሆነ፤

ለ) የፈቃዱ መተላለፍ የባለቤትነት መከማቸትን የማይጨምር ከሆነ፤ እና

ሐ) የፈቃዱ መተላለፍ የብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ ባለፈቃዶች ብዝሃነትን የማይቀንስ ከሆነ፤

5/ በአዋጁና በመመሪያው የተደነገጉት መብትና ግዴታዎች ፈቃዱ ለተላለፈለት ሰው አብረው ይተላለፋሉ፡፡

# ክፍል አራት
# ስለአስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎች

## 37.አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1/ የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅንና አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሰረት ባለስልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት መጣል፤

ሐ) ጥሰት የተፈፀመበትን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ፤

መ) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ፤

2/ ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሲወስን፡-

ሀ) ጣቢያው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊጣልበት እንደሆነና ጥሷል የተባለውን ጉዳይ እንዲያውቅ ማድረግና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፤

ለ) እርምጃው የሚወሰድበትን ምክንያት፣ የማስተካከያ እርምጃውን፣ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን እና የጊዜ ገደብ በፅሁፍ ለባለፈቃዱ ማሳወቅና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ) የጣቢያውን አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታ፣ በጥፋቱ ምክንያት ያገኘውን የገንዘብ ጥቅም፣ ሕግና መመሪዎችን የማክበር እና ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት፤ የገንዘብ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ ፕሮግራሙ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ጊዜ ውስጥ በፕሮግራሙ ላይ ምርመራ ካልተጀመረ አስተዳደራዊ እርምጃው በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

## 38.አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ስልጣን እና ይግባኝ አቀራረብ

1/ የፈቃድ እድሳትን የመከልከል፣ ፈቃድን የማገድ እና የመሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ቦርድ ይሆናል፡፡

2/ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ የገንዘብ ቅጣት የመጣል እና አንድን ፕሮግራም የማገድ ወይም የመሠረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

3/ ባለሥልጣኑ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4/ ቦርዱ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

5/ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 39. በፍርድ ቤት የሚወሰዱ እርምጃዎች

የንግድ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሰረት በፍርድ ቤት የሚከተሉት ሕጋዊ እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላሉ፡-

1/ የስም ማጥፋት ተግባር በመገናኛ ብዙሀን ሲፈፀም በፍትሐብሔር ሀላፊነት እስከ 300,000 ብር (ሦስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የህሊና ጉዳት ካሳ ሊያስቀጣ ይችላል፤

2/ ዓቃቤ ሕጉ በብሔራዊ ደኅንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልጽና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል የብሮድካስት አገልግሎት ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የብሮድካስት አገልግሎቱ እንዳይሰራጭ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ወይም ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ውሳኔ የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት እንዲታገድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ የወንጀል ክስ ሲቀርብ ጥሰት የተፈፀመበትን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ፤

4/ የወንጀል ክስ ሲቀርብ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ፤

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 40.የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍሉ ተግባርና ሃላፊነት

1/ የፈቃድና ምዝገባ ሥራዎች የሚከናወኑት በባለሥልጣኑ ውስጥ በተቋቋመ መደበኛ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ነው፡፡

2/ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍሉ፡-

ሀ) ፈቃድ ጠያቂ አመልካቾች ሞልተው የሚያቀርቡትን የማመልከቻ ቅጽና አባሪ ሰነዶች ይቀበላል፣ ይመዘግባል፣ ለዚሁም ማስረጃ ይሰጣል፤

ለ) የመዘገባቸውን አመልካቾች ዝርዝር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አመቺ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግ ያደርጋል፣ ስለአመልካቾች ከህዝብ አስተያየት ይሰበስባል፤

ሐ) መዝግቦ የተቀበላቸውን የማመልከቻ ቅጾችና አባሪ ሰነዶች እንደዚሁም የሕዝብ አስተያየቶች በአግባቡ ይይዛል፤

መ) በዚህ መመሪያ በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት ዝርዝር ማጣራት በማድረግና በመገምገም ከአስፈላጊ ማብራሪያ ጋር የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ  ሃላፊ ያቀርባል፤

ሠ) መገናኛ ብዙሃን ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀላሉና በቀጥታ ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ሠጪውን ስም፣ አድራሻ፤ የፖስታና የስልክ ቁጥር፣ የኢሜልና የድረ-ገፅ አድራሻ፣ የጣቢያውን ስራ አስኪያጅና ተወካዮች ስምና ስልክ ቁጥር በማጠናቀርና በመመዝገብ በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ ተደራሽ ያደርጋል፤

ረ) ሌሎች ተያያዥ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## 41.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሕግ መሰረት የተሰጡ የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ፈቃዶች እንደፀኑ የሚቆዩ ሲሆን፤ እንደአስፈላጊነቱ በአዋጁ አንቀፅ 44 እና 88 መሠረት ባለፈቃዶች አደረጃጀታቸውን በማሻሻል የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፈቃድ ወይም ልዩ የንግድ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድን ለማሻሻል ሲወስን የሚከተሉትን መረጃዎች ለባለፈቃዱ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የማሻሻያውን ዝርዝር፤

ለ) ለማሻሻል ያስፈለገበትን ዝርዝር ምክንያት፤ እና

ሐ) ማሻሻያው ከመቼ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ፡፡

## 42.የተሻረ መመሪያ

1/ የንግድ ሬዲዮ ፈቃድ አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 01/2000 እና በሳተላይት አማካኝነት የሚሠራጭ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 02/2008 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ትእዛዝ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 43.መመሪያውን ስለማሻሻል

1/ የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል::

2/ ባለሥልጣኑ በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ያረጋግጣል፤ በቦርዱ የፀደቁ መመሪያዎችንም አሳትሞ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 44.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጳጉሜ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 3 ቀን 2014 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ**